የገንዘብ ሚኒስቴር

# ስለ ተቀናሽ ወጪዎች

## የወጣ መመሪያ ቁጥር 5/2011

Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No. 2

መጋቢት 2011 ዓ/ም
አዲስ አበባ

Ministry of
ARCHIVES
2

## ስለ ተቀናሽ ወጪዎች
## የወጣ መመሪያ ቁጥር 5/2011

የገንዘብ ሚኒስትሩ በፌዴራል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 27/1/በ/2፣ አንቀጽ 99/2/፣ በፌዴራል የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 410/2009 30/2/ እና 31 በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ይህ መመሪያ አውጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርእስ**

   ይህ መመሪያ "ስለ ተቀናሽ ወጪዎች የወጣ መመሪያ ቁጥር 5/2011" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በታክስ አስተዳደር አዋጅ ወይም በገቢ ግብር አዋጅ ትርጉም የተሰጠው ቃል በዚህ መመሪያ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለ እንደሆነ በታክስ አስተዳደር አዋጁ ወይም በገቢ ግብር አዋጁ የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

   ሀ. **"አዋጅ"** ማለት የፌደራል ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 ነው፡፡

   ለ. **"ደንብ"** ማለት የፌደራል የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 410/2009 ነው፡፡

   ሐ. **"ባለሥልጣን"** ማለት የገቢዎች ሚኒስቴር ወይም የአዲስ አበባ ከተማና የድሬዳዋ አስተዳደር ገቢዎች ባለስልጣን ናቸው፡፡

   መ. **"ሚኒስቴር"** ማለት የገንዘብ ሚኒስቴር ነው፡፡

3. **የተፈፃሚነት ወሰን**

   ይህ መመሪያ በአዋጁና በደንቡ በተፈቀዱ የሰንጠረዥ ለ እና ሐ ወጪዎች ላይተፈጻሚ ይሆናል፡፡

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2
Ministry of Finance Archives

## ክፍል ሁለት
## ወጪዎች ስለሚቀነሱበት ሁኔታ

### 4. ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ወጪዎች

1. ማንኛውም ወጪ በግብር ከፋዩ ገቢ ውስጥ የተካተቱትን ገቢዎች ለማስገኘት፣ ለስራው ዋስትና ለመስጠት እና ስራውን ለማስቀጠል በግብር ዓመቱ ውስጥ የተደረገ አስፈላጊ የሆነ ወጪ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ እንደ ወጪ ይያዛል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተደነገገው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ አስፈላጊ ወጪዎች የሚከተሉትን ይጨምራል፡

   ሀ. በነፃ በሚጠቀምበት ወይም በተከራየው ህንፃ ስራውን ሲያከናውን ቤቱን በሰጠው ወይም በአከራዩ ስም በሚታወቀው የመብራት፣ የውሃ ወይም የስልክ ቆጣሪ የተጠቀመ እንደሆነ እነዚህ ክፍያዎች በግብር ከፋዩ እንደሚከፈሉ በግልፅ በውል ውስጥ የተካተተ ስለመሆኑ ከተረጋገጠ እና ወጪው የተከፈለበትን ደረሰኝ ኦሪጂናል ካቀረበ፣

   ለ. ለማዘጋጃ ቤት አገልግሎት የተከፈለ ክፍያ፣

   ሐ. የተመዘገበ ተርን ኦቨር ታክስ እና ኤክሳይዝ ታክስ እንዲሁም ተመላሽ ያልተደረገ ወይም በጊዜው ባለመቅረቡ ተመላሽ የማይደረግ የተጨማሪ እሴት ታክስ፣

   መ. የተበላሸ ዕቃ ዋጋ፣ የአገልግሎት ጊዜ ያለፈባቸው እና የተወገዱ እቃዎች ዋጋ እና ለማስወገድ የወጣ ወጪ፡፡

3. ግብር ከፋይ ለንግድ ድርጅት እና መኖሪያ ቤት በአንድ የመብራት፣ የስልክ ወይም የውሃ ቆጣሪ የሚጠቀም በሚሆንበት ጊዜ የመብራት፣ ስልክ እና የውሃ ወጪ በወጪ ተቀናሽ የሚያዘው ከወጪው 75 በመቶ ብቻ ይሆናል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 የተደነገጉት ወጪዎች ከሚያስገኙት ገቢ፣ ለስራው ከሚሰጡት ዋስትና እና ቀጣይነት ጋር ሲነጻጸር ያልተጋነኑና ተመጣጣኝ መሆን አለባቸው፡፡ ወጪዎቹ የተጋነኑ በሚሆኑበት ጊዜ ባለስልጣኑ በተገቢው መረጃ ላይ ተመስርቶ ማስተካከያ ሊያደርግ ይችላል፡፡

5. ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 4 መሰረት ለመወሰን የሚረዳ የአሰራር ሥርዓት አዘጋጅቶ ተፈጻሚ ሊያደርግ ይችላል፡፡

6. አንድ ግብር ከፋይ የንግድ ስራ እንቅስቃሴው በተቋረጠበት በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ወይም ስራ ባላገኘበት ጊዜ ያወጣው ወጪ የማይቀር ወጪ ሆኖ ከተገኘ ገቢ ያላስገኘ ወጪ ቢሆንም በወጪ ተቀናሽ ሊፈቀድለት ይችላል፡፡



Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2
Ministry of Finance ARCHIVES 2

7. ግለሰብ የንግድ ስራ ባለሀብት ከመደበኛ የሥራ ቦታው ከ25 ኪሎ ሜትር በላይ በመሄድ የንግድ ስራውን ለማከናወን በሚያደርገው እንቅስቃሴ ለሚያወጣቸው ወጪዎች ለምግብ እና ለመኝታ ለአንድ ቀን እስከ 1000 ብር፣ ለትራንስፖርት ያወጣው ወጪ በስራ ላይ ባለው የአየር፣ የውሃ እና የየብስ ትራንስፖርት አገልግሎት ዋጋ መሰረት በማስረጃ ተረጋግጦ የወጪ ተቀናሽ የሚፈቀድለት ሆኖ ከዚህ መጠን በላይ የሚያወጣው ወጪ በተቀናሽ ወጪ አይያዝም፡፡

8. በአዋጁ አንቀጽ 27/1/ቀ የተቀመጠ ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ ለግብር ከፋዩ ሠራተኛ የሚከፈል የኃላፊነት አበል ወይም የውክልና አበል ተቀናሽ ሊሆን የሚችለው የንግድ ሥራውን የማስተዋወቅ እና የማሳደግ ሥራ ላይ በሃላፊነት ለሚሰራ ሰራተኛ ወይም የስራ መሪ የተከፈለ ሲሆን ነው፡፡

9. በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ድርጅት በኢትዮጵያ ውስጥ ላለው በቋሚነት ለሚሰራ ድርጅቱ ጥቅም ያደረገውን ትክክለኛ ወጪ ለመተካት በኢትዮጵያ ውስጥ በቋሚነት የሚሰራው ድርጅት የሚፈጽመው ክፍያ ተቀናሽ የሚደረገው ወጪው የንግድ ስራ ገቢ ለማግኘት፣ ለንግዱ ስራ ዋስትና ለመስጠት ወይም የንግድ ሥራውን ለማስቀጠል የተደረገ እና በቋሚነት በሚሠራው ድርጅት ሊሰራ የማይችል ከሆነ ብቻ ነው፡፡

10. የጥቃቅንና አነስተኛ ድርጅት በሥራ ላይ ላሠማራው አባሉ የሚከፍለው ደሞዝ እንደ ወጪ ተቀናሽ ይፈቀድለታል፡፡

11. በዲዛይን ለውጥ ምክንያት ህንጻ ፈርሶ ሲገነባ የፈረሰው ህንፃ የመዝገብ ዋጋ በወጪ ተቀናሽ ይያዛል፡፡

12. የተሽከርካሪ ጎማ የሚሰጠው አገልግሎት ከአንድ አመት ያነሰ እንደሆነ እንደ አላቂ ዕቃ ተቆጥሮ በተቀናሽ ወጪ የሚያዝ ይሆናል፡፡

## 5. <u>የወለድ ወጪ</u>

1. የወለድ ወጪ ሊፈቀድ የሚችለው በብድሩ የተገኘው ገንዘብ ለንግድ ሥራ እንቅስቃሴ መዋሉ ሲረጋገጥ ነው፡፡ ሆኖም የፋይናንስ ተቋማትን ሳይጨምር አንድ ግብር ከፋይ ለተወሰነ የሥራ እንቅስቃሴ የወሰደውን ብድር ለሌላ ዓላማ የሚያውል ወይም ይህንኑ ብድር ለሌላ ተግባር በብድር የሰጠ ከሆነ፣ የሚፈቀድለት ተቀናሽ የወለድ ወጪ ለሌላ ያበደረው ወይም ለሌላ ዓላማ ያዋለው ተቀንሶ ለንግድ ስራው እንቅስቃሴ በዋለው ብድር መጠን ብቻ ይሆናል፡፡

2. አንድ ግብር ከፋይ በዱቤ ለሚገዛው ዕቃ ወይም አገልግሎት ዋጋውን እስኪከፍል ድረስ ወለድ እንደሚከፈልበት ውል የገባ እንደሆነ ለከፈለው የወለድ መጠን በአዋጁ እና በደንቡ መሰረት የወጪ ተቀናሽ ይፈቀድለታል፡፡





በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቤት ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2
Ministry of ARCHIVES 2

3. ግብር ከፋይ ህንጻ ለመገንባት ብድር የወሰደ እንደሆነ፡ ህንጻው እስኪጠናቀቅ ድረስ የተከፈለው ወለድ በእርጅና ተቀናሽ የሚካተት ሆኖ ህንጻው ተገንብቶ ከተጠናቀቀ በኋላ የተከፈለው ወለድ በወጪ ተቀናሽ የሚፈቀድ ይሆናል፡፡

## 6. በምርት ዝግጅትና አቅርቦት ሂደት የሚያጋጥምን ብክነት እንደ ወጪ ስለመያዝ

1. በምርት ዝግጅትና አቅርቦት ሂደት (በብጣሪ፣ በትነት፣ በማቅለጥ፣ በሸርፍራፊ፣ በቆይታ ጊዜ ወዘተ) የሚባክን ምርት የዕቃ መጠን በሚመለከተው የመንግስት አካል በቀረበ ጥናት መሰረት እንደ ወጪ ሊያዝ ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት የተሟላ ጥናት ማግኘት ካልተቻለ ባለስልጣኑ ከግል ተቋማት፣ ከግብር ከፋዮች፣ አግባብነት ያለው አካል ወይም ባለስልጣኑ በሚያደርገው ጥናት መሰረት ወጪ የሚያዝበትን መጠን ሊወስን ይችላል፡፡

3. ለዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 አፈጻጸም ለእያንዳንዱ ምርት መረጃ ሊሰጥ የሚገባውን አግባብነት ያለውን አካል ባለስልጣኑ ይወስናል፡፡

## 7. ተቀናሽ የሚደረግ የመዝናኛ ወጪ

1. የማዕድን ማውጣት እና ፍለጋ ፣ የማኑፋክቸሪንግ እና የግብርናና ሆርቲ ካልቸር ስራ ላይ የተሠማራ ቀጣሪ ለተቀጣሪው በነፃ የሚያቀርበው ምግብ እና መጠጥ ዋጋ በዚህ መመሪያ መሰረት በወጪ የሚያዘው በአንድ ወር የሚያወጣው ወጪ በወሩ ለተቀጣሪዎቹ ካወጣው አጠቃላይ የደሞዝ ወጪ ከ 30% ባልበለጠ መጠን ብቻ ነው፡፡

2. በሆቴሎች፣ በሬስቶራንቶች ወይም በሌሎች የምግብ አገልግሎት በሚያቀርቡ ተቋማት ውስጥ ለተሰማሩ ሰራተኞች ቀጣሪዎች የሚያቀርቡት የምግብ እና መጠጥ ወጪ ተቀናሽ የሚደረገው በአንድ ወር የወጣው ወጪ በወሩ ለተቀጣሪዎቹ ከወጣው አጠቃላይ የደሞዝ ወጪ 20% ባልበለጠ መጠን ብቻ ነው፡፡

3. ለዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 መሰረት የሚፈቀደው የመጠጥ ተቀናሽ ወጪ ምንም የአልኮል ይዘት የሌለው መጠጥ ነው፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 የተገለጹት ተቋማት የምግብ አገልግሎት የሚያቀርቡት በራሳቸው አዘጋጅተው ከሆነ ከምግብ ዝግጅት ጋር በተያያዘ የተደረጉት የግብዓት ወጪዎች በወጪ ተቀባይነት አግኝተው ግብር ከሚከፈልበት ገቢ ላይ ተቀናሽ ሊደረግ የሚችለው ከድርጅቱ በሚቀርብ ህጋዊ ደረሰኝ/ የግዢ ማስረጃ መሰረት ይሆናል፡፡





Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2
ARCHIVES 2 Finance

5. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተገለጹት ተቋማት የምግብ አገልግሎት የሚያቀርቡት በ3ኛ ወገን አማካኝነት ከሆነ ወጪው ተቀባይነት የሚኖረው ስለአቅርቦቱ ከአቅራቢው ጋር የተደረገ ውል፣ አገልግሎቱ ስለመገኘቱ ከድርጅቱ በሚቀርብ ማረጋገጫ እና ለአቅራቢው ገንዘቡ ስለመከፈሉ በሚቀርብ ህጋዊ ደረሰኝ መሰረት ይሆናል፡፡

6. በማዕድን ማውጣት፣ በማኑፋክቸሪንግ እና በግብርና እና በሆርቲካልቸር ስራ የተሠማራ ቀጣሪ ከከተማ ርቆ በሚገኝ ቦታ ለተመደበው ተቀጣሪው በነፃ ለሚያቀርበው የማረፍያ ቤት አገልግሎት ያወጣው ወጪ ተቀናሽ ይፈቀድለታል፡፡

7. ለዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 6 አፈጻጸም " ከከተማ ርቆ የሚገኝ ቦታ" ማለት ቢያንስ ሃያ ሺህ ነዋሪ ካለው የከተማ ወሰን ሰላሳ ኪሎሜትር ርቆ የሚገኝ ሥፍራ ነው፡፡

## 8. <u>የማስታወቂያ ወጪ</u>

1. የንግድ ሥራ ለማስተዋወቅ የተደረገ ወጪ በደንቡ አንቀጽ 31 በተደነገገው መሰረት በወጪነት የሚያዘው፡-

   ሀ. ግብር ከፋይ ምርቱን ወይም አገልግሎቱን ለማስተዋወቅ በተለያዩ ዝግጅቶች ላይ ለሚደረግ የማስተዋወቅ ሥራ በገንዘብ ወይም በምርት ወይም በአገልግሎት የሚፈጽመው ክፍያ በወጪ ተቀናሽ የሚያዘው ከጠቅላላ ገቢው 3 ከመቶ ባልበለጠ መጠን ብቻ ነው፡፡

   ለ. ግብር ከፋይ ምርቱን ወይም አገልግሎቱን ለማስተዋወቅ ለመገናኛ ብዙሃን ወይም ለማስታወቂያ ድርጅት የሚከፍለው ክፍያ ሙሉ በሙሉ በወጪ ተቀናሽነት ይያዛል፡፡

2. ምንም የማስተዋወቅ ስራ ሳይሰራበት የሚሰጥ ገንዘብ፣ ምርት ወይም አገልግሎት ክፍያ በማስታወቂያ ወጪ ተቀናሽ ሆኖ አይያዝም፡፡

## 9. <u>ለበጎ አድራጎት ስራ የሚደረጉ ስጦታዎች ተቀናሽ ወጪ</u>

በአዋጁ አንቀጽ 24/2/ ለበጎ አድራጎት ስራ የሚደረጉ ስጦታዎች በወጪ ተቀናሽነት የሚያዙት የዚህ ዓይነቱ ወጪ ከግብር ከፋዩ ግብር የሚከፈልበት የግብር ዓመቱ ገቢ ከ 10 በመቶ ካልበለጠ ብቻ ነው፡፡ ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም "ግብር የሚከፈልበት የግብር ዓመቱ ገቢ" ማለት ለበጎ አድራጎት ስራ የተደረጉ ስጦታዎች ሳይቀነሱ በሂሳብ መዝገቡ የታየው ግብር የሚከፈልበት ገቢ ነው፡፡

Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2

## 10. ተያያዥ የግብር ግዴታዎች

አንድ ግብር ከፋይ ከከፈለው ክፍያ ሊሰበስበው የሚገባ ከተከፋይ ሒሳብ ተቀንሶ የሚከፈል ግብር /ከተቀጣሪ የስራ ግብር እና በዕቃ ወይም በአገልግሎት ግገር ወቅት ከተከፋይ ሂሳብ የሚቀነስ ግብር/ ቀንሶ ገቢ ያላደረገ ቢሆንም ወጪውን ስለማውጣቱ ከተረጋገጠ ሊከፈል የሚገባውን ግብር፣ ወለድና ቅጣት በማስከፈል ወጪው ሊያዝለት ይገባል፡፡

## 11. ወጪዎችን ስለማከፋፈል

በአዋጁ አንቀጽ 76 እንደተደነገገው ወጪዎችን ለማከፋፈል፡-

1. አንድ ወጪ ከአንድ በላይ የሆኑ የገቢ ዓይነቶችን ለማስገኘት የዋለ እንደሆነ የወጪው ክፍፍል የሚወሰነው ወጪው ጥቅም ላይ በዋለበት ጊዜ ከእያንዳንዱ የገቢ ዓይነት በተገኘ የገቢ ድርሻ ልክ ይሆናል፡፡

2. አንድ ወጪ አንድን ገቢ ለማግኘት እና ለሌሎች ዓላማዎች የዋለ እንደሆነ የወጪው ክፍፍል የሚወሰነው የወጪዎቹ አንጻራዊ ባህርይና መጠን ግምት ውስጥ በማስገባት ገቢ ለማስገኘት እና ለሌላ ዓላማ የዋለበት መጠን እና የወጪ መጠን መጣኔውን በመገመት ገቢ ለማስገኘት የዋለውን መጠን ብቻ በመውሰድ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሶስት
## የእርጅና ተቀናሽ

## 12. በግብር ዓመቱ በሙሉ ጥቅም ላይ ያልዋለ ዋጋው የሚቀንስ ሀብት

በአዋጁ አንቀጽ 25 ንኡስ አንቀጽ 3 እንደተደነገገው አንድ ዋጋው የሚቀንስ ሀብት በግብር ዓመቱ ከፊል ለሆነው የዓመቱ ጊዜ ብቻ በጥቅም ላይ የዋለ እንደሆነ የሚፈቀደው የእርጅና ተቀናሽ ወጪ ከጠቅላላ የዓመቱ የእርጅና ቅናሽ ሂሳብ ላይ ጥቅም ላይ ያልዋለበት የዓመቱ ከፊል ጊዜ ተመጣጣኝ በሆነ መቶኛ ከተቀነሰ በኋላ ያለው ተቀናሽ ወጪ ብቻ ነው፡፡

## 13. ለንግድ ስራ በጥቅም ላይ የዋለው የህንፃ ክፍል

1. በግብር ከፋዩ የተገነባ ህንፃ የእርጅና ቅናሽ መታሰብ የሚጀምረው ሀብቱ የንግድ ስራ ገቢውን ለማስገኘት ለአገልግሎት ዝግጁ ከሆነበትና አገልግሎት መስጠት ከጀመረበት ቀን አንስቶ ሲሆን ተቆጣጣሪው ባለስልጣን ለግብር ከፋዩ የህንፃ ግንባታው ስለመጠናቀቁ የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ከሰጠበት ጊዜ በፊት ሊሆን አይችልም፡፡

2. በአዋጁ አንቀጽ 25 ንኡስ አንቀጽ 4 እና 5 እና በደንቡ አንቀጽ 40 ለእርጅና ተቀናሽ አያያዝ ከጠቅላላው የህንጻ ስፋትና ዋጋ ለንግድ ስራው ጥቅም ላይ

Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2
Ministry of Finance ARCHIVES 2

የዋለው የህንጻው መጠን ዋጋ ተለይቶ ካልቀረበ በወለሉ ስፋት መቶኛ በማስላት ዋጋው ተለይቶ መቅረብ አለበት፡፡

3. ግብር ከፋዩ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት ለይቶ ካላቀረበ ከጠቅላላ የህንጻው ዋጋ ለንግድ ስራው የዋለውን የህንጻው ስፋት መጠን በማስላት ባለስልጣኑ በራሱ ወስኖ ተቀናሽ ያደርጋል፡፡

4. በአዋጁ አንቀጽ 25 ንኡስ አንቀጽ 3 እና 4 መሰረት ጥቅም ላይ የዋለ የህንጻ ክፍል ማለት የህንጻው ክፍል ለሌላ ዓላማ እስካልዋለ ድረስ ግብር ከፋዩ ህንጻውን ለኪራይ አገልግሎት ዝግጁ ያደረገ ከሆነ ህንጻው ባይከራይም ለኪራይ አገልግሎት ጥቅም ላይ እንዳዋለ ተቆጥሮ ከቤት ኪራይ በተገኘ ገቢ ላይ ግብር በሚሰላበት ጊዜ እንደወጪ ተቀናሽ ሊያዝለት ይገባል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 እና 3 የተደነገገው ድንጋጌ ለኪራይ ገቢ ግብርም በተመሳሳይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

6. የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 4 ድንጋጌ ለሌሎች ዋጋቸው የሚቀንስ እና ግዙፋዊ ህለዎት ለሌላቸው ሀብቶች እንደአግባብነቱ ተፈጻሚ ይደረጋል፡፡

## 14. <u>ለእርጅና ቅናሽ መሰረት የሆነ ዋጋ ካልቀረበ በገበያ ዋጋ ስለመወሰን</u>

1. የአንድ ዋጋው የሚቀንስ ሀብት የእርጅና ቅናሽ ለማስላት መሰረት የሆነው የተሰራበት ወይም የተገዛበት ዋጋ የሚገልጽ ሰነድ ታክስ ከፋዩ ማቅረብ ያልቻለ እንደሆነ ባለስልጣኑ በታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 3 መሰረት በሚወስነው የተሰራበት ወይም የተገዛበት የገበያ ዋጋ 70 በመቶ የእርጅና ተቀናሽ ይፈቀድለታል፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ቢኖርም ሀብቱ የተገዛበት ወይም የተሰራበት ዋጋ የተጨማሪ እሴት ታክስ የግብአት ታክስ የተካካሰለት ከሆነ የተካካሰው መጠን በሚፈቀድለት የእርጅና ተቀናሽ ዋጋ ውስጥ አይካተትም፡፡

## 15. <u>የእርጅና ቅናሽ የሚፈቀድበት ሁኔታ</u>

1. ስለ እርጅና የሚደረገውን ቅናሽ ለመወሰን የሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች ሊሟሉ ይገባል፡

   ሀ. የእርጅና ቅናሽ ጊዜያቸውን ያልጨረሱ ንብረቶች ሽያጭ የተከናወነው ግንኙነት ባላቸው ሰዎች መካከል ከሆነና የተላለፈበት ዋጋ ከተጣራ የመዝገብ ዋጋው የሚበልጥ ከሆነ የእርጅና ቅናሽ ለማስላት መሰረት የሚሆነው የተጣራ የመዝገብ ዋጋው ነው፡፡

Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2
Ministry of ARCHIVES 2 Finance

ለ. በታክስ ከፋዩ ስም ላልተመዘገቡ ሀብቶች የእርጅና ተቀናሽ ወጪ አይፈቀድም፡፡

ሐ. በባል ወይም በሚስት ስም የተመዘገበ ህንጻ ለግለሰብ ንግድ ስራ የዋለ እንደሆነ የእርጅና ተቀናሽ ሊፈቀድ የሚችለው ህንጻው ለንግድ ሥራው አገልግሎት እንዲውል፣ የእርጅና ተቀናሽ እንዲጠየቅበትና ህንጻው ሲሸጥ ተገቢውን ግብር እና ታክስ እንዲከፈልበት የባልና የሚስት የስምምነት ሰነድ ሲቀርብ ነው፡፡

2. ለደንቡ አንቀጽ 37 አፈጻጸም ለቀጥተኛ የእርጅና ተቀናሽ የግብር ከፋዩ ዋጋው የሚቀንስ ሀብት ወይም ግዙፋዊ ሀለዎት የሌለው የንግድ ስራ ሀብት ቀሪ ዋጋ ከብር 2000 የሚበልጥ ከሆነ የእርጅና ተቀናሽ ይፈቀድለታል፡፡

3. ማንኛውም የንግድ ሥራ ሀብት የተናጠል ዋጋ ከብር 2000 በታች ከሆነ በአንድ ጊዜ በወጪነት መያዝ አለበት፡፡

4. በዓይነት የሚደረግ የካፒታል ሀብት መዋጮ እና በውርስ ለሚተላለፍ ሀብት የእርጅና ቅናሽ መሰረት በሚተላለፍበት ጊዜ የነበረው የተጣራ የመዝገብ ዋጋ ነው፡፡

## 16. <u>ዋጋው እየቀነሰ የሚሄድ የእርጅና ቅናሽ ዘዴ አቀናነስ</u>

1. ዋጋው እየቀነሰ የሚሄድ የእርጅና መጠን የሚሰላው በግብር ዓመቱ መጀመሪያ በነበረው የተጣራ የመዝገብ ዋጋ ላይ የእርጅና ተቀናሽ መጣኔውን በማስላት ይሆናል፡፡

2. ለዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 አፈጻጸም "በግብር ዓመቱ መጀመሪያ የነበረው የተጣራ የመዝገብ ዋጋ" ማለት ከመጀመሪያው የመዝገብ ዋጋ በየጊዜው የተቀነሱ የእርጅና ተቀናሾች ከተቀነሱ በኋላ የሚገኝ ዋጋ ነው፡፡

## 17. <u>ሀብትን ማስተላለፍ እና በባለቤትነት መያዝ</u>

ለእርጅና ቅናሽ እና የካፒታል ሀብት በማስተላፍ በሚገኝ ጥቅም ላይ ለሚከፈል ግብር አላማ ምዝገባ የሚፈፀምበት ሀብት በሽያጭ፣ በልውውጥ ወይም በስጦታ ሲተላለፍ አስተላላፊው ሀብቱን እንዳስተላላፈ የሚቆጠረው እና የተላለፈለት ሰው ሀብቱን በባለቤትነት እንደያዘ የሚቆጠረው የሽያጭ፣ የልውውጥ ወይም የስጦታ ውሉ፣ ውል ለመዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ዘንድ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ሆኖ የእርጅና ተቀናሽ ሊጠየቅ የሚችለው ሀብቱ የተመዘገበ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡



Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 18. የአሰራር ሥርዓት

ባለሥልጣኑ ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም የሚያግዝ ዝርዝር የአሰራር ሥርአት ሊያወጣ ይችላል፡፡

### 19. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

1. በደብዳቤው የተቀመጠው ጊዜ ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ የተገነቡበት ወይም የተገዙበት ዋጋ የሌላቸው ህንጻዎች እና ሌሎች ግንባታዎች ለእርጅና ተቀናሽ መሰረት የሆነው ዋጋ በተመለከተ በቁጥር 3.5.0/139/08 በቀን 23/09/2008 በባለስልጣኑ የተጻፈ ሰርኩላር ደብዳቤ ተፈጻሚነቱ ይቀጥላል፡፡

2. በምርት ዝግጅትና አቅርቦት ሂደት (በብጣሪ፣ በትነት፣ በማቅለጥ፣ በቆይታ ጊዜ ወዘተ) የሚባክን ምርት በተመለከተ በባለስልጣኑ የተላለፉ ሰርኩላር ደብዳቤዎች በሌላ እስኪተኩ ድረስ ተፈፃሚነታቸው ይቀጥላል፡፡

3. ይህ መመሪያ በሚሸፍናቸው ጉዳዮች ላይ መመሪያው ከመውጣቱ በፊት ውሳኔ ሳያገኙ የቆዩ ጉዳዮች በዚህ መመሪያ መሰረት ውሳኔ ያገኛሉ፡፡

### 20. የተሻረ መመሪያ

ይህንን መመሪያ የሚጻረሩ ሰርኩላር ደብዳቤዎች እና ማንዋሎች ተሽረው በዚህ መመሪያ ተተክተዋል፡፡

### 21. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከሚያዝያ 1 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ መጋቢት 20 ቀን 2011 ዓ.ም

አህመድ ሺዴ

የገንዘብ ሚኒስትር